ኦክላንድ
ወረዳ ጤና ቦርድ

የሕዝብ ጤና

# ሀኪመዎ ልዩ ባለሙያ (ስፔሺያሊስት) ወደአለበት ሆስፒታል ሲያስተላልፈዎት (ሲመራዎት)

Amharic

**ሀኪመዎ ልዩ ባለሙያ (ስፔሺያሊስት) ወደአለበት የሕዝብ ሆስፒታል አስተላልፎዎታል። ይህ አገልግሎት ገንዘብ አያስከፍለዎትም።**

- አስቸኳይ ሳልሆኑ ችግሮች ከልዩ (ስፔሺያሊስት) ክ ሊኒክ ደብዳቤ ለማግኘት ከ 8-12 ሳምንታት ይወ ስዳል። የሚደርሰውም በፖስታ ነው። ልዩ ባለሙያ ንለማየት የሚያስችል ቀጠሮ ለማግኘት ከ6-12 ወራ ት ይወስዳል።

- ደብዳቤው እንደደረሰዎት ማንበበዎን ወይም የሚ ያነብለዎት ሰው እግኝተው ማስነበበዎን ያረጋግጡ ። በተሰጠው የቀጠሮ ስዓት መገኘት የማይችሉ ከ ሆኑ፣ ለክሊኒኩ ደውለው የሰዓት ለውጥ እንዲደ ረግለዎ ያድርጉ።

- ከቀጠሮዎ ቀደም ብሎ እንደ ራጅ የመሳሰሉ አን ዳንድ ምርመራዎችን ማድረግ ያስፈልገዎት ይሆና ል። ሀኪመዎም የጤና ችግረዎን በሚገባ ለይቶ ለ ማወቅ ይረዳው ዘንድ ይህን ምርመራ ቀደም ብ ሎ ማድረገዎ አስፈላጊ ነው።

- አስተርጓሚ የሚያስፈልገዎት ከሆነ፣ እና ለዚህም የተለየ ጥያቄ (ፍላጎት) ለምሳሌ የሴት አስተርጓሚ የሚሹ ከሆነ፣ ቀደም ብለው ለክሊኒኩ ማሳወቀ ዎን ያረጋግጡ።

- በቀጠሮዎ የማይሄዱ (የማይገኙ) ከሆነ፣ ሌላ እዲስቀጠሮ ለማግኘት ረዥም ጊዜ ይወስዳል። በማንኛውም ምክንያት ወደ ቀጠሮዎ ይማይሄዱ ከሆኑ፣ለክሊኒኩ ደውለው ቀ ጠሮዎን በማሰረዝ ሌላ አዲስ ቀጠሮ ያስይዙ።

- የልዩ ባለሙው ሀኪም (ዶክተር)፣ ለቤተሰብ ሀኪመዎ ሪ ፖርት ይልካል። ይህም ሪፖርት ለቤተሰብ ሀኪመዎ የማ ደርሰው ልዩ ባለሙያውን ሀኪም ካዩከ2-3 ሳምንታት በ ሚሆን ጊዜ ውስጥ ነው። ከአንድ በላይ የቤተሰብ ሀኪ ም ካለዎት፣ የልዩ ባለሙያው ሪፖት የሚሄደው ወደባለ ሙያው ሳስተላለፉዎት ሀኪም ስለሚሆን ችግረዎን በትክ ክል ለይቶ ለማወቅ የሚያስቸግር ይሆናል።

- የክሊኒክ ቀጠሮን ለማመቻቸት ቅድመ-መሰናዶ ማድረግን ይጠይቃል። ለምሳሌም፣ ልጆችዎን የሚጠብለዎትና የሚን ከባከብለዎት ሰው ማመቻቸተዎን፣ በአውቶቡስ የሚጓዙ ከሆነ፣ ወይም ሌላ የሚወስደዎት ሰው ካለዎት ለዚሁ ጉዞዎ በቂ ጊዜ ያለዎት መሆኑን ማረጋገጥ የመሳሰሉት ን ማለት ነው። የቅዱስ ዮሃንስ (ሴንት ጆን) የህክምና ማመላለሻ አውቶቡስ ከቤተዎ መጥቶ እንዲዎስደዎት ቀ ደም ብለው ቀጠሮማስያዝ(ቡክ ማድረግ) ይችላሉ። የአመላ ላሽ አውቶቡሱን አንድ ቀን ቀደም ብለው ማዘዝ (ቡክ ማድረግ) ያስፈልገዎታል (ኢንፎርሜሽን ተያይዟል)። ክሊኒ ኩ የት እንደሆነ የማያውቁ ከሆኑ፣ ፈልጎ ለማግኘት እ ንዲቻል የግማሽ ሰዓት እንዲኖር ማድረግ ይኖርበዎታል።

- በርካታ ባለቀጠሮዎች ስለሚኖሩና እርሰዎም ተራዎን ማ ሳለፍ ስለማይፈልጉ በሰዓቱ መገኘት አስፈላጊ ነው።

- በሆስፒታል ውስጥ እንዲተኙ ከተደረጉም፣ የተለየ ምግብ የሚያስፈልገዎት ከሆኑ ይህንኑ የአስተዳደር ጸሐፊው እ ንዲያውቅ ማድረገዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

Amharic